# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦገስት 1-31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከሴፕቴምበር 1-30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2023
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....... 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 3

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....... 4

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 4

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ....... 5

ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 5

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 6

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ....... 6

ጠባይ አዝማሚያ ....... 6

ካርታ 6 ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የሚኖረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 8

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 9


# እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ወር የክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በሀገሪቱ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ ስፍራዎች ላይ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ በመቀጠል ዝናቡ ከክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መጠናከር ጋር ተያይዞ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ደቡብ ምዕራብ በደቡብ ከፍተኛ ስፍራዎች እና መካከለኛው እንዲሁም ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚስፋፋበት ጊዜ ነው፡፡

ባለፈው ኦገስት ወር የመጀመሪያው አስር ቀናት የዝናቡ ስርጭት በምዕራብ፣በደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ እንዲሁም ደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ በሁለተኛው አስር ቀናት ግን በሰሜን ምስራቅ፣በምስራቅ እንዲሁም በመካከለኛ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የመቀነስ አዝማሚያ የታየበት ሲሆን በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት ነበር፡፡ በሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ደግሞ የዝናቡ ስርጭት ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በሀገሪቱ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ አከባቢዎች ላይ ከሁለተኛዉ አስር ቀናት የተሻለ እና የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት ነበር፡፡ በኦገስት ወር ዉስጥ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 37.4፣38.0፣ በሃዋሳ 50.8፣በባህር ዳር 43.2፣55.0፣30.9፣35.2፣ በኮምቦልቻ 42.9፣ በደብረ ማርቆስ 31.0፣40.5፣ በጎሬ 42.5፣48.8፣ በጅማ 34.2፣34.1፣ በመተሃራ 37.0፣31.8፣ በነቀምቴ 63.8፣ በባሌ ሮቤ 36.4፣ በአዲስ አበባ ኦብዘርቫቶሪ 31.0፣37.0፣ በሃሮማያ 38.0፣በአለም ከተማ 42.0፣ በአልጌ 30.0፣ በአምባ ማሪያም 63.2፣37.6፣ በአርጆ 42.6፣36.4፣32.6፣ በአይከል 43.0፣35.6፣ በባቲ 31.5፣46.0፣በቻግኒ 46.8፣ በደብረ ታቦር 71.9፣ 39.4፣30.2፣ እንዋሪ 40.1፣ በፊቼ 34.9፣ በጋቲራ 31.8፣33.7፣31.7፣35.4፣31.8፣ በጊምቢ 43.1፣ በማሻ 50.4፣40.4፣60.4፣76.4፣ በሜኤሶ 40.3፣በሳዉላ 36.3፣ በሻምቡ 42.7፣ 57.8፣58.0 እንዲሁም በወረኢሉ 30.4 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በሌላ በኩል የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቧል (ምስል 2)፡፡

ከ40 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ


ባለፈው የኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣አርሲ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፤ከአማራ ክልል ሰሜን፣ምዕራብ እና ማዕከላዊ ጎንደር፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣አዊ ዞን፣ዋግምራ፣ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ከጋምቤላ ክልል ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ኑዌር፣አኙዋክ እና ማጃንግ ዞኖች፣ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ካማሺ፣መተከል ዞን፣ከደቡብ ምዕራብ እትዮጵያ ምዕራብ ኦሞ፣ባስኬቶ፣ቤንች ሸኮ፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ከምባታ ጠንባሮ፣ኮንታ ልዩ ወረዳ፣ሀዲያ፣ጉራጌ፣ስልጤ፣ሀላባ እና ጌዲኦ፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የዳውሮ እና የወላይታ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ፋፋን እና ኤረር ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 1፣2 እና 4፤ በድሬዳዋ፣ ሐረሪ እና በአዲስ አበባ፣ ላይ ከ10-530 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-30 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፈው የኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ ክልል ሰሜን፣ማዕከላዊና እና ደቡብ ጎንደር፣ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣አዊ ዞን፣ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ቄለም ወለጋ፣ቡኖ በደሌ፣ኢሉባቦር፣ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ምዕራብ ሸዋ፣ቦረና እና ባሌ፣ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ እና ከማሺ ፣ከጋምቤላ ክልል ኑዌር እና አኙዋክ ዞኖች፣ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቤንች ሸኮ፣ምዕራብ ኦሞ፣ሀረሪ፣ድሬዳዋ እና በአዲስ አበባ ላይ መደበኛ ዝናብ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል። በተጨማሪም ከሱማሌ ክልል ሲቲና የፋፈን ዞኖች፣ከኦሮሚያ ክልል አርሲ፣ አርሲ ምዕራብ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ እና የባሌ ዞኖች፤ የአፋር ክልል


ዞኖች፤ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ዋግዕምራ፤ከጋምቤላ ክልል የኑዌር ዞን እና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል ዞን ላይ ከመደበኛው በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፈው የኦገስት ወር ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ የሆኑት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ በመጀመሪያው እና ሦስተኛው አስራ አንድ ቀናት የዝናቡ ስርጭት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ እንዲሁም ደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ በሁለተኛው አስር ቀናት ግን በምስራቅ እንዲሁም መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የመቀነስ አዝማሚያ የታየበት ቢሆንም በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻል እንዲሁም ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን ውሃ ከማቅረብ አንጻር ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከሰብል ልማት አንጻርም ቀደም ሲል በሚያዚያና ግንቦት ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት እንዲሁም ዘግይተዉ ተዘርተው በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉት እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ እና ጤፍ ለመሳሰሉት ሰብሎች፣ የጥራጥሬ እህሎችና የቅባት እህሎች እንዲሁም ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በተጨማሪም ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች በመጠን ረገድ አነስተኛም ቢሆን ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት መሟላት በጎ ጎን ነበረው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ በዚህም ምክንያት ማሳ ላይ ዉሃ መተኛትና ቅጽበታዊ ጎርፍ በተወሰኑ ቦታዎች በመከሰቱ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ባሉ ሰብሎች፣ በአፈር ጥበቃ ሥራ እንዲሁም በሰው እና በንብረት ላይ መጠነኛ ጉዳት ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ኦገስት ወር  አብዛኛው አባይ ባሮአኮቦ፤ ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የላይኛው ተከዜ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣  በጥቂት የላይኛው ዋቢ.ሸበሌ እና ገናሌ እንዲሁም አፋር ደናከል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ በጣም ከፍተኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው። ከዚሁ ጋር ተያየዞ በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የነበረው የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ወደ ግድቦች እና የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን በመጨመር አስተዋፆ ነበረው ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ሴፕቴምበር የክረምት ወቅት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተዳከመና እየቀነሰ የሚሄድበት ወር ነው፡፡ ይሁን እንጂ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ያልሆኑ አከባቢዎች ማለትም የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ፡፡ የወቅቱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሴፕቴምበር በመጀመሪያው አሥር ቀናት ጀምሮ ከሰሜን ምሥራቅና ከሰሜን ኢትዮጵያ ቀስ በቀስ እየተዳከመ በመሄድ በምዕራብ፤ በደቡብ ምዕራብና በመካከለኛው

የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ይወሰናሉ፡፡ በወሩ መጨረሻ ሳምንት ደግሞ የሰሜን ምሥራቅ፤ የምሥራቅና የመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች በበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ ሥር መሆን ይጀምራሉ፡፡

በመጪው የሴፕቴምበር ወር በፀሐይ ሃይል ታግዘው ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቦታዎች ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የክረምቱ ዝናብ አወጣጥ ከአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ መደበኛ ፈሩን ተከትሎ የሚወጣ ሲሆንና ከሰሜን ምስራቅ፤ ምስራቅና መከካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ቀድሞ እንደሚወጣ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሴፕቴምበር ወር የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና የመካከለኛዉ የትግራይ ክልል ዞኖች፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ የምዕራብ፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን ሸዋ፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ ፤ ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋና የሸዋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፤ ቡኖ በደሌ፤ አዲስ አበባ፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የወላይታ፤ የዳውሮ፤ የጋሞ፤ የጎፋና የጌዲዮ ዞኖች፤ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብና የሲዳማ ክልል ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ፣ የአርሲና የምዕራብ አርሲ ዞኖች፣ የባሌና የምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ የጎጂና የምዕራብ ጉጂ ዞኖች እንዲሁም ጥቂት የቦረና ዞኖች ፤ ድሬዳዋ እና ሀረሪ፤ ከሶማሌ ክልል ፋፈን፣ ሲቲ፣ የኖጎብና የጃራር ዞኖች፤ የጋምቤላ ክልል፤ ከአፋር ክልል የዞን 1፣ 3 እና 4፤ የደቡብና የምስራቅ ትግራይ ዞኖች፤የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ሀይል በመታገዝ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች ላይ በመነሳትና ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡




ካርታ 6 ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የሚኖረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የሴፕቴምበር ወር የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖራቸው ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቀጣይ ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ በተለይም ዘግይተዉ ለተዘሩና በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙትም ሆነ ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉት ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት እንዲሁም በክረምት ወቅት መጨረሻ በአፈር ውሰጥ በተከማቸው እርጥበት በመታገዝ በደጋማው አካባቢ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእፅዋት ልምላሜና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት መሻሻል እና በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ባለፉት የክረምት ወራት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅ ሆነው በሰነበቱትና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ለሆኑት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች የጎላ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ በሌላም በኩል ከመደበኛ በላይ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ በአንዳንድ ቦታዎች እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም ከሰብል ጥበቃ አንፃርም ሆነ ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር ተዳምሮ ለፀረ ሰብል ተባይ አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ስለሚችል የሚመለከተው ክፍል የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-

አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የክረምቱ ዝናብ አወጣጥ ከአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ መደበኛ ፈሩን ተከትሎ የሚወጣ ቢሆንም ከሰሜን ምስራቅ፤ ምስራቅና መከካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ቀድሞ እንደሚወጣ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተለይም እርጥበቱ ቀድሞ በሚወጣባቸው ቦታዎች ላይ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀምና የተለያዩ የዉሃ ማከማቻና መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ በማድረግ በእርጥበት እጥረት ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ የሚያስችል የጥንቃቄ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ሴፕተምበር ወር የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ይኖራል፡፡ በተጨማሪም የክረምቱ እርጥበት መጠን ከሞላ ጎደል ከመደበኛዉ ጋር ተቀራራቢ በሆነ ጊዜ ከአብዛኛዎቹ የወቅቱ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶዎች ላይ እንደሚወጣ እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ የላይኛው አዋሽ፣ እንዲሁም ገናሌዳዋ አዋሳኝ የተፋሰሱ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የተሻለ እርጥበት መጠን ሊያገኙ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎችን ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛው አፋር ዳናክል እና የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞጊቤ፣ በመካከለኛው አዋሽ፣ በታችኛው ባሮአኮቦ፣ በጥቂት የላይኛው ተከዜ አነስተኛ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡